# የብልጽግና ፓርቲ

# የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር/ የአሰራር መመሪያ

## (በማዕከላዊ ኮሚቴ የጸደቀ)

ጥር /2016 ዓ.ም

# የብልጽግና ፓርቲ የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር የአሰራር መመሪያ ቁጥር ----- /2015

በብልጽግና ፓርቲ አንደኛ ጉባኤ በጸደቀው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ከተቋቋሙት የፓርቲው መዋቅር አንዱ የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን በመሆኑ

በመተዳደሪያ ደንቡ የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ተግባራትና ሃላፊነት የተደነገገ በመሆኑ፤

ለኮሚሽኑ በተሰጠው ተግባራትና ሃላፊነት መሠረት ዝርዝር የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 23(6)(ረ) መሰረት የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ይህን መመሪያ አጽድቋል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

- ይህ መመሪያ "የብልጽግና ፓርቲ የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር የአሰራር መመሪያ ቁጥር……/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

1. "ፓርቲ" ፓርቲ ማለት የብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና) ነው፡፡
2. "ኮሚሽን" ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በየደረጃው የተቋቋመው የፓርቲው የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን ማለት ነው፤
3. "መተዳደሪያ-ደንብ" ማለት የብልጽግና ፓርቲ በአንደኛው መደበኛ ጉባኤው ያፀደቀው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ማለት ነው፣

# የቀጠለ -----------------

4. “ቁጥጥር” ማለት የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች ተፈጻሚነት በየደረጃው በሚገኙ የኮሚሽኑ አካላት የሚያደርግ ቁጥጥር(ድጋፋዊ ክትትል) ማለት ነው፣
5. “ኢንስፔክሽን” ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች አፈጻጸም እንዲሁም ከአባላት በሚቀርቡ ጥቆማዎች ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን(ምርመራ) ማለት ነው፡፡

# የቀጠለ ----------------

6. “የፓርቲ ሥነ ምግባር” ማለት በፓርቲው ጉዳዮች በነጻነትና በእኩልነት የመሳተፍ፣ በየትኛውም መድረክ የመሰለውን ሀሳብ ነፃ ሆኖ የማራመድና የመከራከር፣ ማወቅ የሚገባውን በፓርቲው ጉዳይ የመጠየቅና መረጃ የማግኘት፣ በፓርቲው ውስጥ የሚታዩ ጉድለቶች ላይ እንዲስተካከሉ ሂስ የማቅረብ፣ የሚከሰቱ የሃሳብ ልዩነቶችን ወይም አለመግባባቶችን በበቂ ውይይት በማድረግ በፓርቲው የአሰራር መርሆዎች ተከትሎ መፍታት እና ከበቂ ውይይት በኋላ የብዙሃን ድምጽ ላገኘ ውሳኔ ተገዢ በመሆን የመተግበር ግዴታን የሚያጠቃልል ነው፤

# የቀጠለ ----------------

7. "መልካም ሥነ ምግባር" ማለት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተደነገጉ የአባልነት ግዴታ፣ የፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና የአሰራር መርሆዎችን በጥብቅ መፈፀም እንዲሁም በህብረተሰቡ የሚስማማባቸውን የግብረገብ እሴቶችን ማክበርና መልካም ተግባራትን በመፈጸም አርአያ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፤
8. "የሥነ ምግባር ብልሹነት" ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱትን የፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና የአሰራር መርሆዎች እና ህብረተሰቡ የሚስማማባቸው የግብረገብ እሴቶችን የሚቃረን ድርጊት ፈጽሞ መገኘት ነው፤

# የቀጠለ ----------------

9 “የፖለቲካ ጥራት” ማለት ፓርቲው የሚመራበት የመደመር እሳቤ እና የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ የጻና አቋም ያለው፣ የህዝቦች የብሄር፣ የእምነትና የጾታ ልዩነትን በእምነት ተቀብሎ ለአንድነት፣ እኩልነትና የጋራ ተጠቃሚነት መትጋት እንዲሁም የፓርቲውን ዓላማ ከሚያደናቅፉ ከጽንፈኝነትና አክራርነት በአመለካከትና ተግባር ነጻ በመሆን የፓርቲን ተልዕኮ መፈፀም ማለት ነው፤

10 “ሙስናን መዋጋት” ማለት የፓርቲ አባላት፣ አመራርና አካላት የአገሪቱን የፀረ-ሙስና ህግ የማክበር፣ ማስከበር፣ የፓርቲውና የመንግስትን ንብረትና ሀብት በአግባቡ መያዝን፣ ከሙስናን አድሎ ድርጊቶች መራቅ፣ ሙስናን መጠየፍ፣ መሰኞችን መታገል፣ ያልተገባ ጥቅም አለመፈለግ፣ በሙስና አስከፍነት ላይ በቀጣይነት ግንዛቤ መፍጠር እና ለሙስና በር የሚከፍቱ ቀዳዳዎችን ለይቶ መዝጋት ማለት ነው፤

# የቀጠለ ---------------

11. ”ቅሬታ” ማለት የፓርቲ አባላትና አመራሮች ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና የአሰራር መመሪያዎች ውጭ በደል ተፈጸመብን ብለው ሲያምኑ በየደረጃው ለሚገኘው የፓርቲ አካላት የሚያቀርቡት ቅሬታ ማለት ነው፣

12. “አቤቱታ” ማለት በየደረጃው ላለው የፓርቲ መዋቅር ቅሬታ አቅርቦ በውሳኔው ባልረኩ አባላት በየደረጃው ላሉት የኮሚሽን መዋቅር የሚቀርብ አቤቱታ ማለት ነው፣

13. “የፓርቲ ሀብት እና ንብረት” ማለት ፓርቲው የሚያስተዳድረው ገንዘብና ቁሳቁስ ማለት ነው፡፡

LOREM IPSUM DOLOR SIT AMET

# የቀጠለ ----------------

14. “መረጃ” ማለት የፓርቲው ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ እቅዶች፣ ሪፖርቶች፣ ቃለ ጉባዔዎች፣ ውሳኔዎች፣ የአባላት ፕሮፋይል፣ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ ለፓርቲው ስራዎች እንዲያገለግሉ የታተሙና ያልታተሙ የፓርቲው ሠነዶች ማለት ነው፣

15. “አባል” ማለት የፓርቲውን ፕሮግራም ተቀብሎ በመተዳደርያ ደንቡ መሰረት የፓርቲ ሙሉ አባል ወይም እጩ አባል ማለት ነው፡፡

16.“አመራር” ማለት የፓርቲውን ፕሮግራም ለማስፈጸም በየደረጃው ባለው የፓርቲው መዋቅሮች በሃላፊነት የተመደበ ወይም የተመረጠ ማለት ነው፡፡

17. በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትን ፆታም ይመለከታል፣

# 1. ዓላማ

1. የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ መርሆዎችና እሴቶችን በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸው ክትትል የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት፣
2. ፓርቲው ውስጥ የፖለቲካ ጥራት፣ የአባላት ሥነ ምግባር ጤናማነት እና ሙስና ላይ በተገቢው ትግል መደረጉን ለማረጋገጥ ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ እና
3. የፓርቲው ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውና ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትል ለማድረግ፣
4. የአካላትና አባላት መብቶችና ጥቅሞች መከበሩንና ከአባላት የሚቀርቡ አቤቱታ በሚያቀርቡበት ሂደቶች አሰራር ለመዘርጋት ነው፡፡

LOREM IPSUM DOLOR SIT AMET

# 1. የተፈጻሚነት ወሰን

- በየደረጃው በሚገኘው የፓርቲ መዋቅር፣ አመራር፣ አካላትና አባላት ላይ ሁሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የቁጥጥር የአሰራር ስርዓት

## 5. የቁጥጥር ስራው የትኩረት መስኮች፣

በየደረጃው ቁጥጥር የሚካሄድባቸው የትኩረት መስኮች የሚከተሉት ጉዳዮች ናቸው፡፡

1. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸው ክትትል ማድረግ፣
2. የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ ምግባር ጤናማነት መሻሻሉን ለማረጋገጥ፣
3. በፓርቲ ሙስና ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት መደረጉን ክትትል ማድረግ፣
4. የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መጠበቃቸውንና ስራ ላይ ስለመዋላቸው ቁጥጥር ማድረግ፣

5.የፓርቲ የአባልነት መዋጮ በወቅቱና በትክክል መሰብሰቡን ለመቆጣጠር፣

6. የፓርቲው አካላትና አባላት መብቶች፣ ጥቅሞች መከበራቸውን ለመከታተል እና

7.ከአባላት የሚቀርቡ አቤቱታዎች መመርመርና የእርምት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ ናቸው፡፡

# 6. ቁጥጥር የሚደረግበት አግባብ

## 1. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች ሥራ ላይ መዋሉን ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት፤

ሀ) በመተደደሪያ ደንቡና መመሪያዎች ላይ ለአባላትና አመራር ግንዛቤ ስለመፈጠሩ፣

ለ) የፓርቲው መተደደሪያ ደንብና መመሪያዎች ተደራሽ ስለመሆናቸው፣

ሐ) የፓርቲው አባላት መተደደሪያ ደንቡንና መመሪያዎችን በአግባቡ ስለማወቃቸው፣

መ) በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ መዋቅር በመተደደሪያ ደንቡንና መመሪያዎችን በመከተል ሥራዎችን ስለመፈጸሙ፣

ሠ) የመተደደሪያ ደንቡና መመሪያዎች አሰራር ጥሰት ወይም ግድፈት ሲያጋጥም የአሰራር ሥርዓት ጠብቆ የእርምት ርምጃ በወቅቱ ስለመወሰዳቸው፣

ረ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተሰሩ ስራዎች ለአባላት ሪፖርት ቀርቦ ስለመገምገማቸው።፡

# 2.የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራት መሻሻሉ የሚረጋገጥበት ሥርዓት፤

ሀ) በየወቅቱ የአባላትና አመራሩ ፓለቲካዊ አመለካከት ሊያጎለብቱ የሚችሉ ጽሁፎች በማዘጋጀት ውይይት እየተደረገ ስለመሆኑ፣

ለ) ከማዕከል የሚላኩ የመወያያ ልሳናትንና መወያያ ሰነዶች በፓርቲው የሥራ ቋንቋ ተዘጋጅተው በሚወርዱ ላይ በየደረጃው ውይይት ስለመደረጉ፣

ሐ) ፓርቲው የሚመራበት የመደመር እሳቤ፣ መርሆች፣ እሴቶች እና የፖለቲካ ፕሮግራም አቋሞች ላይ ግልጽነት ስለመፈጠሩ፣

መ) የፓርቲውን ዓላማ ከሚያደናቅፉ ከጽንፈኝነትና አክራርነት/ዋልታ ረገጥ/ አመለካከትና ተግባር አባሉ እና አመራሩ የጸዳ መሆኑና በሚታዩት ጉድለቶች ላይ የሃሳብ ትግል ስለመደረጉ፣

# የቀጠለ ----------------

ሠ) ከማዕከል የሚላኩ የመወያያ ልሳናትንና መወያያ ሰነዶች በፓርቲው የሥራ ቋንቋ ተዘጋጅተው በሚወርዱት ላይ በየደረጃው ውይይት ስለመደረጉ፣

ረ) የፖለቲካ አመለካከት ችግር በሚታይባቸው አባላት ላይ የአሰራር ሥርዓት ጠብቆ የእርምት ርምጃ ስለመወሰዱ፣

ሰ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተሰሩ ስራዎች ለአባላት ሪፖርት ቀርቦ ስለመገምገማቸው።

# 3.በፓርቲው የስነ ምግባር ጤናማነት መሻሻሉን የሚረጋገጥበት ሥርዓት፤

ሀ) የመንግስትና የፓርቲውን ሕጎችና ውሳኔዎች ስለመከበራቸው፣

ለ) በመተዳደሪያ ደንቡ በተደነገጉ የአባልነት ግዴታ፣ መርሆዎች፣ እሴቶችና የአሰራር መርሆዎች ላይ ግልጽት ስለመፈጠሩና በጥብቅ ዲስፕሊን ስለመከበሩ፣

ሐ) በህብረተሰቡ የሚስማማባቸውን የግብረገብ እሴቶችን ማክበርና መልካም ተግባራትን በመፈጸም አርአያ ሆኖ ስለመገኘት፣

# የቀጠለ ----------------

መ)አባላትና አመራር የፓርቲውን ክብርና ሞገስ ከሚያጎድፉ ተግባርትና ባህርያት ስለመቆጠባቸው፣

ሠ) የሥነ-ምግባር ብልሹነት በሚታይባቸው አባላት ላይ የአሰራር ሥርዓትን ጠብቆ የእርምት ርምጃ ስለመወሰዱ፣

ረ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተሰሩ ስራዎች ለአባላት ሪፖርት ቀርቦ ስለመገምገማቸው::

# 4.በፓርቲ ውስጥ የሙስና ትግል ስለመደረጉ ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት፣

ሀ) የፓርቲ አባላት፣ አመራርና አካላት የአገሪቱን የፀረ-ሙስና ህግ አውቀው ስለማክበራቸውና ስለማስከበራቸው፣

ለ) አባሉና አመራሩ የፓርቲውና የመንግስትን ንብረትና ሀብት በአግባቡ ስለመያዙ፣ ለሙስና በር የሚከፍቱ ቀዳዳዎችን ለይቶ ስለመዝጋቱ፣

ሐ) ስለ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በሚመለከት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በየደረጃው እንዲፈጠሩ ስለመደረጉ፣

መ) ሙስናን ለመዋጋት የሚደረገው ትግል በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲ አካላት ዕቅድ፣ ሪፖርት፣ ድጋፋዊ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ አካል ስለመሆኑ፣

# የቀጠለ -----------------

ሠ) በፓርቲው ውስጥ ሙስናን አድሎ ድርጊቶች መራቅ፣ ሙስናን መጠየፍ፣ ሙሰኞችን መታገል፣ ያልተገባ ጥቅም አለመፈለግ፣ በሙስና አስከፍነት ላይ የጠራ አመለካከት ስለመያዙና የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ስለመደረጉ፣

ረ) ከሙስናና ብልሹ አሰራር የጸዳ ተቋም መገንባት ለቻሉ አባላት፣ አመራርና አካላት እውቅና ስለመሰጠቱ፣

ሰ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተሰሩ ስራዎች ለአባላት ሪፖርት ቀርቦ ስለመገምገማቸው፡፡

## 5.የፓርቲው አካላትና አባላት መብቶችና ጥቅሞች መከበራቸውን ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት፣

ሀ) የፓርቲ አባላት በየደረጃው በሚካሄዱ የአካላት ምርጫዎች የመምረጥና የመመረጥ መብት ስለመረጋገጡ፣

ለ) አባላት በፓርቲ ጉዳዮች በሚኖሩ መድረኮች በነጻነትና በእኩልነት በውይይት የመሳተፍ፣ በየትኛውም መድረክ የመሰለውን ሀሳብ ነፃ ሆኖ የማራመድና የመከራከር፣ ማወቅ የሚገባውን በፓርቲው ጉዳይ የመጠየቅና መረጃ የማግኘት መብት የተረጋገጠ ስለመሆኑ፣

ሐ) በፓርቲ ውስጥ የሚሰጡ ስልጠናዎች፣ የትምህርት ዕድሎች፣ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ግልጽነት ባለሁ አግባብ ስለመተግባረቸው፣

# የቀጠለ ----------------

ሐ) በፓርቲው ውስጥ የሚታዩ ጉድለቶች ላይ እንዲስተካከሉ ሂስ የማቅረብ፣ የሚከሰቱ የሃሳብ ልዩነቶችን ወይም አለመግባባቶችን በበቂ ውይይት በማድረግ በፓርቲው የአሰራር መርሆዎች ተከትሎ የመፍታት ባህል ስለማዳበሩ፣

መ) በፓርቲ መድረኮች በቂ ውይይት ተደርጎበት የብዙሃን ድምጽ ያገኘ ውሳኔ ወይም ጉዳይ አባላት፣ አመራርና አካላት ተገዢ በመሆን በጥብቅ ዲስፕሊን የመተግበር ግዴታ እየተወጡ ስለመሆናቸው፣

ሠ) የብዙሃን ውሳኔ በማያከብሩ አባላትና አመራር ላይ የሚወሰድ የእርምት ርምጃ ስለመኖሩ፣

ረ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተሰሩ ስራዎች ለአባላት ሪፖርት ቀርቦ ስለመገምገማቸው::

# 6.ከአባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎች መመርመርና የውሳኔ ሃሳብ የሚቀርብበት ሥርዓት፤

ሀ) አባላትና አመራር ቅሬታውን የሚያቀርብበት አሰራር ስለመኖሩ፣

ለ) ከአባላት የቀረበ ቅሬታ በሚመለከተው አካል ታይቶ በጋራ አመራር ውሳኔ የሚሰጥ ስለመሆኑ፣

ሐ) በጋራ አመራር የተደረሰበት ውሳኔ ቅሬታ ላቀረበው አባል ወይም አመራር ውሳኔ በጽሑፍ የሚሰጥ ስለመሆኑ፣

መ) አባላትና አመራር ቅሬታ እንዳያቀርቡ የሚያግድ ተጽዕኖዎች አለመኖራቸው፣

ሠ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተሰሩ ስራዎች ለአባላት ሪፖርት ቀርቦ ስለመገምገማቸው::

# 7. የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መጠበቃቸውና ስራ ላይ መዋላቸው ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት፤

ሀ) የፓርቲ ገንዘብ፣ ንብረቶችና ሰነዶች በአግባቡ ስለመጠበቃቸው፣

ለ) የፓርቲው ገንዘብና ንብረት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በፓርቲው የአሰራር መመሪያዎች ተከትለው ስራ ላይ ስለመዋላቸው፣

ሐ) የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በየወቅቱ በውስጥና በውጭ ኦዲት ስለመደረጋቸው፣

መ) በገንዘብና በዐይነት ከፓርቲው ደጋፊዎች የሚሰበሰብ እና ልዩ ልዩ ገቢዎች በአግባቡ ታውቆ አሟጦ ገቢ ስለመሆናቸው፣

ሠ) የፓርቲው ሀብትና ንብረት ተገምቶ በውል ስለመታወቁ፣

# የቀጠለ -----------------

ረ) በተሰጠው የኦዲት ግኝት መሰረት የማስተካከያ እርምጃዎች ስለመወሰዳቸው፣

ሰ) የአባላት መረጃ በአግባቡ በዘመናዊ መልክ እንዲደራጅ መደረጉንና ወቅታዊ ስለመሆኑ፣

ሸ) የፓርቲ ሰነዶች በአግባቡ ተሰንደው እና ተመዝግበው ስለመያዛቸው፣

ቀ) የፓርቲው አመራርና አባላት ከቦታ ቦታ ስዛወሩ በእጃቸው የሚገኘውን ንብረትና ሰነድ ስለማስረከባቸው፣

በ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተሰሩ ስራዎች ለአባላት ሪፖርት ቀርቦ ስለመገምገማቸው።

# 8. የፓርቲ የአባልነት መዋጮ በወቅቱና በትክክል መሰብሰቡን ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት፤

ሀ) በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ አባላት በሙሉ የአባልነት መዋጮ በትክክል ታቅዶ ተሟጦ በመሰብሰብ ገቢ ስለመደረጉ፣

ለ) የአባልነት መዋጮ ለከፈሉት አባላት ደረሰኝ በወቅቱ እየተሰጣቸው ስለመሆኑ፣

ሐ) የአባልነት መዋጮ የማይከፍሉ አባላት ላይ አሰራር ጠብቆ የእርምት ርምጃ ስለመወሰዱ፣

መ) የአባላት መዋጮ በየወቅቱ በውስጥና በውጭ ኦዲት ስለመደረጋቸው፣

ሠ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተሰሩ ስራዎች ለአባላት ሪፖርት ቀርቦ ስለመገምገማቸው፡፡

# 9የቁጥጥር አሰራር

ሀ. የማስፈጸሚያ እቅድ እና ቼክ ሊስት ማዘጋጀት፣

ለ. ቁጥጥር በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ ብቃት ያላቸዉ አባላትን በመለየትና ኦረንቴሽን መስጠት፣

ሐ. የቁጥጥር ስምሪት ስራዉ ገጽ ለገጽ፣ በሰነድ ምልከታ፣ በመስክ ምልከተና የቃለ-መጠይቅ ዘዴዎች መጠቀም፣

መ. የቁጥጥር ሥራው አፈጻጸም ሪፖርት የማዘጋጀት፣ በጋራ የመገምገም፣ መረጃዎችን የማደራጀት፣ የመተንተን በየደረጃው ላሉ ለሚመለከታቸው አካላት በተለያዩ ዘዴዎች ግብረ-መልስ ይሰጣል፣

# 10. የቁጥጥር ተሳታፊ አካላት መቋቋምና ተግባርና ሃላፊነት

1. **የቡድን አመሰራረት**

ሀ) በቁጥጥር የሚሳተፉ የኮሚሽኑ አባላት እና እንደ አስፈላጊነቱ ደጋፊዎች ተሳታፊ ይሆናሉ፤

ለ) ኮሚቴ ሲቋቋም ሰብሳቢ፣ ጸሐፍና አባላት ተለይተው ምደባ ይደረጋል፣

ሐ) ለስራው የሚሰማራው ቡድን እና አባላት ብዛት እንደ ስራው ስፋትና ጥበት እንዲሁም ወቅታዊነት እየታዩ የሚወሰን ይሆናል፡፡

መ) ኮሚሽኑ ለቁጥጥር ስራዉ የሰዉ ሀይል ከክልል፣ ክልሎች ከዞን፣ ዞኖች ከወረዳ እና ወረዳዎች ከመ/ድርጅቶች የሰዉ ሀይል መድበው ሊያሰማሩ ይችላሉ፣

# 1.የቡድን ተግባርና ሃላፊነት

ሀ) የስራ ቢጋር እና ቼል ሊስት ማዘጋጀት፣

ለ) የተሰጣቸውን ተልዕኮ በሃላፊነት፣ በጥራት፣ በተመደበው ጊዜ በአግባቡ የማፈጸም፣

ሐ) በየደረጃው ለሚመለከተው አካል በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ አጭር ግብረ-መልስ የመስጠት እና

መ) የተሟላ ሪፖርት እና ምክረ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ናቸው፡፡

# 11. የቁጥጥር ስራዎች ግብረ-መልስ ሂደት

1. በመሰረታዊ ድርጅት ደረጃ የተካሄደውን ቁጥጥር ውጤት የመሰረታዊ ድርጅት ኮሚቴ ለወረዳ ኮሚሽን ጽ/ቤት ሪፖርቱን ከምክረ ሀሳብ ጋር ያቀርባል፣

2. በወረዳ ደረጃ የተካሄደ ቁጥጥር ዉጤት ከምክረ ሀሳብ ጋር ለወረዳ የፓርቲ ጽ/ቤትና ለዞን የኮሚሽን ጽ/ቤት ይልካል፣

3. በዞን ደረጃ የተደረገዉን የቁጥጥር ሥራ ዉጤትና ምክረ ሀሳብ ለዞን የፓርቲጽ/ቤትና ለክልል የኮሚሽን ጽ/ቤት ይሰጣል፣

# የቀጠለ ----------------

4. በክልል ደረጃ የተካሄደውን የቁጥጥር ስራ ውጤት ለማእከላዊ የኮሚሽን ጽ/ቤትና ለክልሉ ፓርቲ ጽ/ቤት ከምክረ ሀሳብ ጋር ይቀርባል፣

5. በማዕከል ደረጃ የተካሄደውን የቁጥጥር ስራ ውጤትና ምክረ ሃሳብ መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዩችን በመለየት ለፓርቲዉ ዋና ጽ/ቤት ይሰጣል፣

6. በቁጥጥር ግኝቱ የተለዩ ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምረው ቤደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት እንዲጠቀሙ ይደረጋል፣

# 12.የቁጥጥር ስራዎች ሪፖርት አቀራረብ

1.ስምሪት ለሰጠው አካል በቁጥጥር ዕቅዱና ቼክ-ሊስቱ መሰረት ሪፖርት ተጠናቅሮ ይቀርባል፡፡

2.ሪፖርት በሚደራጅበት ወቅት የምስልና ተንቀሳቃሽ ምስሎች አሊያም በድምጽ የተደገፈ ቅጂ ሲሆን መረጃዎችን ከጽሁፍ ሪፖርቱ ጋር አያይዞ ይቀርባል፣

3.በመድረክ ለሚደረግ የሪፖርት ግምገማ በፓዎር ፖይንት ተዘጋጅቶ ይቀርባል፣

# 13. የቁጥጥር ስራዎች ግምገማ መድረክ አካሄድ

1. በየደረጃው የቁጥጥር ቡድኑን ያሰማራው አካል የተሰሩ ስራዎችን የጋራ መድረክ በማዘጋጀት መገምገም ይኖርበታል፡፡
2. በመድረኩ የቁጥጥር ቡድኑ ሰብሳቢ ሪፖርት የሚቀርብ ይሆናል።
3. የቁጥጥር ቡድኑ አባላት በግምገማ ወቅት ለሚነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ማብራሪያ ይሰጣሉ።

# 14. እውቅናና ተጠያቂነት

1. በተግባር አፈጻጸማቸው በተሻለ ደረጃ መፈጸም የቻሉ አካላት እንዲሁም የተለያዩ ፈጠራዎችን ተጠቅመው ውጤታማ መሆን የቻሉት እውቅና ይሰጣቸዋል፡፡
2. የቁጥጥር ሥራን በዚህ መመሪያ መሰረት በማይፈጽሙ አመራርና አካላት ላይ የአሰራር ስርዓት ተከትሎ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## 15. የቁጥጥር ስራዎች ሚከናወኑበት የጊዜ ሰሌዳ

1. በማዕከል ኮሚሽን በዓመት ሁለት ጊዜ ቁጥጥር ሥራ ይካሄዳል፣
2. በክልል ኮሚሽን በዓመት ሶስት ጊዜ ቁጥጥር ሥራ ይካሄዳል፣
3. በዞን ደረጃ በአመት አራት ጊዜ ይሰራል፣
4. በወረዳ ደረጃ በአመት አራት ጊዜ ይከናወናል፣
5. በቀበሌ ወይም መሠረታዊ ድርጅት ደረጃ በአመት አራት ጊዜ ይካሄዳል፡

# ክፍል ሶስት

# የኢንስፔክሽን /ምርመራ/ ስራዎች የአሰራር ስርዓት

## 16. የኢንስፔክሽን ሥራ የሚካሄድባቸው የትኩረት መስኮች

1. በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም አስተባባሪ ኮሚቴዎች እንዲጣራ የሚጠየቁ ጉዳዮች፣
2. ኮሚሽኑ በተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ምርመራ እንዲደረግ በተወሰኑ ጉዳዮች እና
3. ከማንኛዉም የፓርቲ አባላት ወይም አካላት የሚቀርቡ ጥቆማዎች ሲኖሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

# 17. የኢንስፔክሽን ሂደት

## 1. ቅድመ ኢንስፔክሽን

ሀ/ ጥያቄ ወይም ጥቆማ እንደ ቀረበ የኮሚሽኑ ሥራ አመራር ኮሚቴ በኮሚሽኑ የስልጣን ወሰን ውስጥ የሚወድቅ መሆኑን አረጋግጦ ለኮሚሽኑ አቅርቦ ያስፈቅዳል፡፡

ለ/ በኮሚሽኑ ከጸደቀ በኋላ በጽ/ቤት አማካይነት ዕቅድና ቼክ-ሊስት ይዘጋጃል፤

ሐ/ የምርመራ ቡድን በማቋቋም ኦሬንቴሽንና ስምርት ይሰጣል፤

መ/ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የሰው ሀይል፤ የሎጂስትክስና ሌሎች ግብዓቶችን የማሟላት ስራዎች በኮሚሽኑ ጽ/ቤት በኩል የሚፈጸም ይሆናል፤

## 2. ኢንስፔክሽ ትግበራ

ሀ/ የቀረበውን ጥቆማ መነሻ በማድረግ ወደ ተለዩ ስፍራዎች በመሄድ የምርመራ ስራ ይጀመራል፤

ለ/ የምርመራ ስራ ለመጀመር በየደረጃው ከሚገኙ የፓርቲ ጽ/ቤት አመራሮች ወይም ከኮሚሽኑ አመራሮች ጋር ለስራው ተባባሪ እንዲሆኑ ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ስራ ይገባል፤

ሐ/ የዕቅዱ ማስፈጸሚያ ስልቶችን ተከትሎ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን የማጣራትና የመመርመር ስራዎችን ይሰራል፡፡

# የቀጠለ ----------------

መ/ መረጃና ማስረጃዎች በሚደራጁበት ወቅት በሀርድ ኮፒ አሊያም በምስልና በድምጽ የተደገፈ መሆን ይገባዋል የሚል እሳቤ ካለው የጠቋሚዎችን መብት ለመጠበቅ ሲባል ፍቃደኛ በሆኑ አካላት ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፣

ሠ/ የምርመራ ቡድኑን ያሰማረው የኮሚሽኑ አካል ለቡድኑ አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ያጋጠማቸው ችግር ካላ እንዲፈታ ያደርጋል፣

ረ/ የምርመራ ስራ እንደተጠናቀቀ የምርመራ ቡድኑ ኃላፊነት በተሞላበትና በሚስጥር በኢንስፔክሽኑ ዕቅድና ቼክ-ሊስት መሰረት ሙሉ ሪፖርት እና ምክረ ሃሳብ ያዘጋጃል፡፡

# 3. ድህረ-ኢንስፔክሽን

ሀ/ የምርመራ ቡድኑ ያጠናቀረውን ሪፖርት እና የተሰበሰበውን መረጃና ማስረጃ በማደራጀት ስምሪት ለሰጠው አካል ሪፖርት ያቀርባል፣

ለ/ የምርመራ ቡድኑን ያሰማረው የኮሚሽኑ አካልና የምርመራ ቡድኑ በጋራ ሪፖርቱ ይገመገማል፡፡

ሐ/ በየደረጃው የሚገኘው የኮሚሽኑ ወይም ኮሚቴ ሰብሳቢ ጉዳዩን እንደ ሚስጥራዊነቱ ሁኔታ ተገንዝቦ ለኮሚሽኑ ግኝት/የዉሳኔ ሀሳቡን ቀርቦ ይጸድቃል፣

# የቀጠለ ----------------

መ) ሰብሳቢው በኮሚሽን ደረጃ የጸደቀውን ግኝት/ምክር ሀሳብ የምርመራ ጥያቄ ላቀረበ ወይም ለሚመለከተው የፓርቲ አካል የምርመራው ግኝት ምክረ ሃሳብ የያዘ ሪፖርት ያቀርባል፣ ስለማስረከቡ መተማመኛ ይወስዳል፡፡

ሠ/ በየደረጃዉ የሚገኘው የኮሚሽኑ የምክረ ሃሳቡ አፈጻጸም ይከታተላል፣

ረ) በየደረጃው በሚደረጉ ኮንፈረንሶች የተደረሰበት አፈጻጸም ለአባላት የሪፖርት አካል ሆኖ ይቀርባል፡፡

# 18. የይጣራልኝ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት

1. ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ የይጣራል ጥያቄ በጽሁፍ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. የይጣራል ጥያቄ በማዕከላዊ ኮሚቴ ወይም በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከሆነ ከውሳኔው ጋር በማያያዝ በፓርቲው ጽ/ቤት ሃላፊ ፊርማ መሆን ይገባል፡፡

# የቀጠለ ----------------

3. የይጣራል ጥያቄ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አስተባበሪ ኮሚቴ የተወሰነ መሆኑን የሚያሳይ ውሳኔ ጋር በማያያዝ በጽ/ቤት ሃላፊ ፊርማ መሆን ይገባል፡፡
4. የይጣራል ጥያቄ ያቀረበለት የኮሚሽኑ አካላት ስለመቀበሉ ለአቅራቢው አካል ማስረጃ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## 19. የጥቆማ አቀራረብ ሥርዓት

1) ሙስና ወይም ብልሹ አሠራር ተፈጽሟል ብሎ የሚያምን ማንኛውም አባል በስልክ፣ በአካል፣ በኢ-ሜይል፣ በፋክስና በፖስታ ቤት ጥቆማውን ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይቻላል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀረብ ጥቆማ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርባቸዋል፤

ሀ) የጥቆማ አቅራቢ ሙሉ ስምና አድራሻ፣

ለ) የተፈጸመው ሙስና ወይም ብልሹ አሠራር ምን እንደሆነ፣

ሐ) ሙስና ወይም ብልሹ አሠራር የፈጸመ አካል ማንነት፣

መ) ሙስና ወይም ብልሹ አሠራር የተፈፀመበት የፓርቲ መዋቅር፣

# የቀጠለ ----------------

3. የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ጥቆማዎቹን ከተቀበሉ በኋላ የቀረቡት ጥቆማዎች እውነትም የሙስና ወይም ብልሹ አሰራር ስለመሆናቸውና በኮሚሽኑ የስልጣን ክልል የሚወድቁ ስለመሆናቸው መጣራት ይኖርበታል፣
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ጥቆማ የተቀበለ የኮሚሽን ጽ/ቤት ለጥቆማ አቅራቢው ማስረጃ መስጠት ይኖርበታል፣
5. የቀረበው ጥቆማ ሙስና ወይም ብልሹ አሰራር መሆናቸው ከተረጋገጠና በኮሚሽኑ የስልጣን ክልል የሚወድቁ ከሆኑ እንዲጣራ ለኮሚሽኑ ቀርቦ መፍቀድ ይኖርበታል፡፡

# የቀጠለ -----------------

6. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15(1) (ሀ) መሠረት በኮሚሽኑ የተፈቀደና በበቂ ማስረጃዎች በተደገፉትና ምርመራቸው የተጠናቀቁ ጉዳዮች ሪፖርትና ምክረ ሀሳብ በኮሚሽኑ ጸድቆ ለሚመለከተው የፓርቲ መዋቅር ይላካል፤

7. ጠቋሚዎች ያቀረቧቸው ጥቆማዎች ያሉበትን ደረጃ ኮሚሽኑን ጠይቀው ምላሽ ማግኘት ይችላሉ፤

8. ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ከመጋቢት 3/2014 ዓ.ም በፊት ተፈጸሙ በተባሉ ጉዳዮች ላይ ጥቆማ አይቀበልም::

9. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገገ ቢኖርም፤ ከዚህ ቀደም ተጀምረው በሂደት ያ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ተፈጻሚነት ያገኛሉ::

# 20. የሚካሄዱ የኢንስፔክሽን አይነቶች

## 1.መደበኛ

ሀ) አመታዊ የፓርቲ ስራዎችን ዕቅድ መነሻ በማድረግ ራሱን የቻለ ዕቅድና ቼክ-ሊስት በማዘጋጀት ይሰራል፡፡

ለ) የኢንስፔክሽን ግኝቶችን በየደረጃው ለሚገኝ የፓርቲ ጽ/ቤት አመራሮች በተደራጀ መልኩ ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡ በግብረ-መልሱ መሰረት የእርምት ተግባራት ስለመፈጸማቸው በሱፐርቪዥን የክትትል ስራዎች ይተገበራሉ፡፡

## 1.ድንገተኛ

ሀ) ከፓርቲ አካላት በሚቀርበው የይጣራልኝ ጥያቄ ወይም ከአባላት ጥቆማ መሰረት ድንገተኛ ኢንስፔክሽን ይካሄዳል፣

ለ) የድንገተኛ ኢንስፔክሽን ግኝቶች ተደራጅተው ሪፖርት ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

# 21. የኢንስፔክሽን ተደራጊዎች ግዴታ

i. የኢንስፔክሽን ስራ ለሚያካሄዱ የምርመራ ቡድን አስፈላጊውን ሁሉ የማመቻቸት ሃላፊነት አለባቸው፡፡

ii. በምርመራ ቡድኑ የሚጠየቁ ማንኛውንም መረጃ፣ ማስረጃና ሰነዶች የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፤

iii. የምርመራ ቡድኑ ስራውን ነጻና ገለልተኛ ሆኖ እንዲያከናውን እገዛ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

iv. የምርመራ ቡድኑን ስራዎችን ለማደናቀፍ መሞከር ወይም ተጽእኖ መፍጠር በፓርቲው ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ተጠያቂ ያደርጋል፡፡

# 22. የኢንስፔክተሮች ወይም የምርመራ ቡድን ሃላፊነት

1. ስነ-ምግባር

ሀ) ሚስጥር መጠበቅ፣

ለ) የተሰጠውን ተልዕኮ በሃላፊነት ስሜት መፈጸም፣

ሐ) የፓርቲውን መርሆዎችና እሴቶች ማክበር፣

መ) የምርመራ ግኝቶችን ከሚመለከተው አካል ውጪ ሪፖርት አለማድረግ ናቸው።

1. ተጠያቂነት

ከላይ የተደነገጉ ስነ ምግባሮችን የጣሰ የምርመራ ቡድን አባል በፓርቲው ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 23. የኮሚሽኑና የፓርቲው ግንኙነት

ከፓርቲ የበላይ አካላት ጋር የሚኖረው የግንኙነት አግባብ የሚከተለው ይሆናል፤

1) **በማዕከል ደረጃ** ኮሚሽኑ እንዳስፈላጊነቱ በ6 ወር አንድ ጊዜ ከፓርቲው ጽ/ቤት የበላይ አመራር ጋር በመሰረታዊ የፓርቲውና የኮሚሽኑን ጉዳዮች አስመልክቶ በጋራ የሚወያዩበት መድረክ ይኖራል።

2) **በክልል ደረጃ** የክልል የኮሚሽን በ3 ወር አንዴ ከክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር የጋራ ውይይት ያደርጋሉ፤

3) **በዞን ደረጃ** የዞን ኮሚሽን ከዞኑ አስተባባሪ ኮሚቴ ወይም ከፓርቲ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በሁለት ወር አንድ ጊዜ በጋራ መድረክ ይኖራቸዋል፤

4. **በወረዳ ደረጃ** ኮሚሽኑ ከወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ ወይም ከፓርቲ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በየወሩ የጋራ ውይይት ያካሂዳሉ፣
5. **በመሰረታዊ ድርጅት ደረጃ** የመሰረታዊ ድርጅት (ቀበሌ) ኮሚሽን በወር አንድ ጊዜ ከቀበሌ አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር በጋራ ውይይት ያካሂዳሉ፣
6. በዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ (1) - (5) የተደነገገ ቢኖርም እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ጉዳዩች ሲኖሩ ባጠረ ጊዜ መድረኮች ሊፈጠሩ ይችላሉ፣
7. የኮሚሽኑ አባላት በፓርቲ አባላት ላይ በሚወሰኑ የዲስፕሊን እርምጃዎች ላይ ድምጽ አይሰጡም።

# 24. የፓርቲ ጽ/ቤቶች ኃላፊነት

1. ኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ የማገዝና የመደገፍ፣
2. ለስራው የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል፣ በጀትና ሎጅስቲክ ማሟላት፣የማመቻቸት፣
3. በየደረጃው የጋራ የውይይት መድረኮች እንዲፈጠሩ የማድረግ፣
4. የኮሚሽን አመራሮች ስምርት በጋራ ምክክር የማድረግ፣
5. በፓርቲው እቅድ፣ ሪፖርት፣ የውይይት ሰነዶች ኮሚሽን የማጠናከር ተግባራት መካተቱንና በየደረጃው በሚካሄዱ ኮንፈረንሶች የኮሚሽኑ እቅድና ሪፖርት መቅረቡን የማረጋገጥ እና
6. በኮሚሽኑ የሚሰጡ ምክረ ሀሳቦችን የመፈጸም ሃላፊነት አለባቸው፡፡

# 25. የኮሚሽኑ ሥልጣን

1. በማንኛውም ጊዜ በየደረጃው የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር የማካሄድ፣
2. የፓርቲውን አመራሮችና አባላት የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ተግባራት የማስማራት እና
3. የፓርቲውን አካላት፣ አመራርና አባላት አግኝቶ የማወያየት፣ የፓርቲውን ሰነዶች ለሥራ ሲፈልግ የማግኘት እና
4. በየደረጃው ለፓርቲው መዋቅር የተሰጡ የውሳኔ ምክረ ሀሳቦችን አፈጻጸም የመከታተል ሥልጣን አለው፡፡

## 26. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የፓርቲ አካላት፣ አመራርና አባላት ይህን መመሪያ የማክበር፣ የማስከበርና ለተፈጻሚነቱ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡

## 27. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ልማዳዊ አሰራር ወይም ሕግ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 28. መመሪውን ስለማሻሻል፣

ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኮሚሽኑ ሃሳብ አቅራቢነት በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 26. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በማዕከላዊ ኮሚቴ ከጸደቀበት ሐምሌ -------- ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

መስከረም 2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

የብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

# እናመሰግናለን